የሰ.መ.ቁ 229608

ቀን መጋቢት 29 2015ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡ እድገት እርምጃ እድር ማህበር ጠ ጋሻሁን ፈየራ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡ 1ኛ. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮልፌ ቀ/ክ/ከተማ የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽ/ቤት -አልቀረቡም

2ኛ. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን - ነ/ፈ ሙሉጌታ ጉተታ - ቀረቡ

3ኛ. የኮልፌ ቀ/ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ 258076 በ24/3/14ዓ.ም በሰጠው ብይን እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 217574 በ8/10/14ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት በ21/10/14ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች በስር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረበው ክስ በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ 24 ቀበሌ 17 በአሁኑ ወረዳ 7 የቤ/ቁ አዲስ የቦታው ስፋት 46,945 ካ.ሜ አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሱትን ቤት እና ይዞታ አመልካች ሐምሌ 12 ቀን 1963ዓ.ም ከአቶ ዘውዴ ለማ እና ተክሌ ዋቆ በብር 14,113.00(አስራ አራት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሶስት ብር) ገዝተን

በማይንቀሳቀስ ንብረት ባለመብትነት ማስተላለፊያ ክፍል ተመዝግቦ ስሙ ወደ አመልካች ዞሯል፡፡ አመልካች በዚህ ቦታ ላይ ወቅቱን የጠበቀ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጠው በተለያየ ግዜ ለክፍለ ከተማው የሰነድ አልባ ይዞታዎች መስተንግዶ ፕሮጀክት ጽ/ቤት አቤቱታ ሲያቀርብ የቆየ እና ፈጣን ምላሽ ሊያገኝ ያልቻለ ቢሆንም በአሁኑ ሰአት ዘመናዊ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሊሰጥበት የቦታው ልኬት ስራው ተጠናቆ ካርታ ለመውሰድ በመጠባበቅ ላይ እያለን 1ኛ. የአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ልማት ማኔጅመንት ቢሮ የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ግዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት፤ 2ኛ. የኮልፌ ቀ/ክ/ከተማ የመሬት ልማት እና ማኔጅመንት አስተዳደር የሽግግር ግዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሰራተኞቻቸውን ወደ አመልካች ይዞታ በመላክ ሰራተኞቹም ቦታው የመንግስት ነው፤ ማህበሩንም አይመለከትም፤ መብትም የለውም፤ ልታስረክቡ ይገባል በማለታቸው አመልካች በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ 240234 በሆነው የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርቦ ፍ/ቤቱ በ2/10/09ዓ.ም በዋለው ችሎት ተቋማቱ እየፈጠሩ ያሉት ሁከት እንዲወገድ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህን ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ተከሳሾቹ ከአድራጎታቸው ባለመቆጠባቸው አመልካች የተሰጠውን ፍርድ መሰረት በማድረግ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ 280824 በሆነ የአፈጻጸም ፋይል ከፍቶ ችሎቱም በ3/3/12ዓ.ም በዋለው ችሎት ክርክር የተነሳበት ይዞታ በማንኛውም ሁኔታ ወደ 3ኛ ሰው እንዳይተላለፍ እንዳይከለል የእግድ ትእዛዝ ሰጥቶበታል፡፡

የፍርድ ቤቱ የእግድ ትእዛዝ ሳይነሳ ጸንቶ እያለ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በ11/3/12ዓ.ም በተጻፈ የውል ቁጥር 23/2012 በሆነ የአመልካች ይዞታ በሆነው 46,945ካ.ሜ ይዞታ ላይ የሊዝ ውል ተዋውለው በ23/3/12ዓ.ም 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ የአመልካችን ይዞታ ጨምሮ ለ2ኛ ተጠሪ ያስረከበው ከመሆኑም በላይ በ30/3/12ዓ.ም ቁጥሩ በተገለጸ ደብዳቤ 3ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ ካርታ ሰርቶ እንዲሰጥ አዞ 3ኛ ተጠሪም የክርክሩ ተካፋይ የነበረ እና በይዞታው ላይ እግድ ያለ መሆኑን እያወቀ ለ2ኛ ተጠሪ በ6/4/12ዓ.ም 3ኛ ተጠሪ የአመልካችን ይዞታ ጭምር በማካተት በ100,983 ካ.ሜ ቦታ ላይ ካርታ ሰርቶ አስጥቷል፡፡ 2ኛ ተጠሪም ካርታውን ከተቀበለ በኋላ የአፈጻጸም ክርክር መኖሩን እና የእግድ ትእዛዝ መሰጠቱን አውቆ እና ተረድቶ እግዱ እንዲነሳለት አፈጻጸሙን ለያዘው ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርቦ የሊዝ ውሉን እና ካርታውን ጭምር በማስረጃነት አቅርቦ የተከራከረ ቢሆንም ከህግ የመነጨ መብት ሳይኖረው ይዞታው በህግ አግባብ እንደተላለፈለት አስመስሎ ያቀረበውን አቤቱታ ፍ/ቤቱ ውድቅ አድርጎበታል፡፡ በተጨማሪም በይዞታው ላይ ማናቸውም ግንባታም ሆነ የቁፋሮ ስራ እንዳይከናወን በ11/1012ዓ.ም በኮ.መ.ቁ 280824 በሰጠው ትእዛዝ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ በመጣስ ለ2ኛ ተጠሪ በ11/3/12ዓ.ም የአመልካችን ይዞታ 46,945ካ.ሜ ጨምሮ በ100,983 ካ.ሜ ላይ የሰጠው የሊዝ ውል እንዲሰረዝልኝ፤ 3ኛ ተጠሪም ከ1ኛ ተጠሪ የተሰጠውን የሊዝ ውልና ካርታ እንዲሰጥ የተጻፈለትን ደብዳቤ መነሻ አድርጎ የአመልካች ይዞታ እግድ ያለበት መሆኑን እያወቀ ለ2ኛ ተጠሪ በ6/4/12ዓ.ም ሰርቶ የሰጠው ካርታ አላግባብ ስለሆነ

ካርታውን እንዲያመክን ውሳኔ እንዲሰጥልን፣ 2ኛ ተጠሪ ከህግ ውጪ ያገኘውን ካርታ መሰረት አድርጎ የአመልካችን ይዞታ አጥሮ እና ቆፍሮ የያዘውን 46,945ካ.ሜ አጥሩን አፍርሶ የቆፈረውን ቦታ ወደነበረበት መልሶ ይዞታውን ለአመልካች እንዲያስረክብ ውሳኔ እንዲሰጥልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪዎች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አመልካች ባቀረበው ክስ ላይ የጠቀሰውን ይዞታ በ12/11/63ዓ.ም ከአቶ ዘውዴ ለማ እና ከአቶ ተክሌ ዋቆ መግዛቱን በመግለጽ ማስረጃ ያቀረበ ሲሆን ይህም በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 3(1፤2፤3) መሰረት አዋጁ ከጸናበት ግዜ ጀምሮ የከተማ ቦታ የመንግስት ንብረት ነው፡፡ ማንም ቤተሰብ ግለሰብ ወይም ድርጅት የከተማ ቦታን በግል ባለሀብትነት ለመያዝ አይችልም፡፡ ለከተማ ቦታም ካሳ አይከፈልም በማለት ደንግጓል፡፡ መሬቱ የመንግስት ሲሆን በውል ሰጪ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ባንክ እና ማስተላለፍ ጽ/ቤት እና በውል ተቀባይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን በውል ቁጥር 23/2012/2012 በ1/3/12ዓ.ም በኮልፌቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 07 ውስጥ የሚገኘውን ቦታ ደረጃ 3/2 የቦታው ስፋት 100,983ካ.ሜ ለጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ የአካባቢው መጠሪያ ስም ቤተል ሰፈር አካባቢ በሊዝ ለ2ኛ ተጠሪ አስተላልፏል፡፡ ስለሆነም ክርክር ያስነሳው መሬት የመንግስት ስለሆነ በፍ/ብ/ስ/ስህ/ቁ 33(2) መሰረት አመልካች መብትና ጥቅም የለውም ተብሎ ክሱ ውድቅ እንዲሆን፡፡

ክርክር ያስነሳው ቦታ ባዶ ክፍት የነበረና በአዲስ አበባ መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ለአሽከርካሪዎች ስልጠናና መፈተኛ ሲውል ቆይቶ ግንባታ በወቅቱ መጀመር ባለመቻላቸው በከተማ መስተዳደሩ ውሳኔ ለጋራ መኖሪያ ቤት እንዲውል የተደረገ ነው፡፡ አመልካች በቦታው መብት ያለው ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ የአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 5(1) መሰረት ማንኛውም ግለሰብ ከሊዝ ስሪት ውጪ ክፍት የመንግስት ይዞታን መያዝ እንደማይችል ደንግጓል፡፡ ስለሆነም አመልካች ማስረጃ ባላቀረበበት ሁኔታ የመፋለም ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም የለውም ተብሎ እንዲወሰን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍርድቤቱም ክሱን ከሰማ በኋላ ጭብጥ በመያዝ በተጠሪዎች የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መርምሮ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግስት ንብረት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 47/67 ከታወጀበት ቀን ጀምሮ የከተማ ቦታ በግለሰቦች በርስትነት የሚያዝ እንዳልሆነ እንዲሁም ግለሰቦች በከተማ ቦታ ላይ የመጠቀም ወይም በይዞታ መብት ሊኖራቸው የሚችለው በሚመለከተው የመንግስት አካል በህጋዊ መንገድ ሲሰጣቸው ወይም ባለመብት መሆናቸውን ከዚሁ አካል ሲያረጋግጡ እንደሆነ ደንግጓል፡፡ ይህም ከአዋጁ መውጣት በፊት የተሰጡ የይዞታ ማረጋገጫዎች እና ሰነዶች ባለመብት እንደማያደርጉ የሚያስረዳ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በቦታው ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንደሌለው በተለያየ ግዜ ለክፍለከተማው የሰነድ አልባ ይዞታዎች መስተንግዶ ፕሮጀክት ጽ/ቤት አቤቱታ ሲያቀርብ የቆየ መሆኑን

በክሱ ያረጋገጠው ነው፡፡ አመልካች ይዞታውን በእጁ አድርጎ ሲገለገል እንደነበር እና ለረጅም ግዜ ግብር እየገበረ እንደነበር ቢከራከርም ይህን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ አመልካች ክርክር ባስነሳው የከተማ ቦታ ላይ ክስ ለመመስረት የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት አዋጁ ከወጣ በኋላ የመንግስት አካል በሰጠው ይዞታ ወይም የመጠቀም መብት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ሆኖም አመልካች ከአዋጁ በኋላ ከመንግስት አካል የተሰጠው ይዞታ ወይም የመጠቀም መብት ማረጋገጫ ሳይኖረውና በእጁ ባላደረገው ይዞታ ክስ ያቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 33(2) መብትና ጥቅም ሳይኖረው የቀረበ ክስ በመሆኑ በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 245(1) መሰረት በሰጠው ብይን ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች ከላይ በተገለጸው ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ብይን እና ትእዛዝ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 33(2) መሰረት ከሳሽ ባቀረበው ክስ ላይ መብትና ጥቅም የለውም ተብሎ የሚወሰነው ክስ ባቀረበበት ጉዳይ ላይ መብት ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ ሳያቀርብ ሲቀር ነው፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ ባቀረበበት ንብረት ላይ መብትና ጥቅም ያለው ስለመሆኑ የተለያዩ ማስረጃዎችን(በሰበር አቤቱታው ላይ የተዘረዘሩ) ከክሱ ጋር አያይዞ አቅርቦ ሳለ የስር ፍ/ቤቱ አመልካች ክሱን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የለውም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ የሰጠው ብይን እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት መብትና ጥቅም የማይንቀሳቀስ ንብረት ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በማቅረብ ብቻ እንደሚረጋገጥ አድርጎ ብይን የሰጠ ሲሆን ይህም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 36320(ቅጽ 9) በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ክስ ለማቅረብ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ማቅረብ ግዴታ አለመሆኑን እና ባለይዞታነት በሌላ መንገድ ሊረጋገጥ እንደሚችል ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውጪ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚሉ ሌሎች በስር ፍ/ቤቶች ብይን እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል የሚልበትን ነጥቦች በመዘርዘር እንዲሻር፤ 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠው የሊዝ ውል እንዲሰረዝ፤ 3ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠው ካርታ እንዲመክን እና 2ኛ ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ላይ የጀመረውን አጥር አፍርሶ እንዲያነሳ እንዲሁም ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለኝ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ይዞታ በ1963ዓ.ም ገዝቶ ስሙን ወደራሱ ያዛወረ መሆኑን፤ ከአስተዳደር አካል ጋር ክርክር አድርጎ ሁከት እንዲወገድ ውሳኔ ማስጠቱን እና ካርታ እንዲሰጠው በተለያየ ግዜ ጥያቄ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን በመግለጽ ያቀረበውን ክስ ስር ፍ/ቤት አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ የሌለው በመሆኑ ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የለውም በማለት ክሱን በብይን ውድቅ በማድረግ የወሰነበትን አግባብነት ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 33(2) እና ሰበር መ.ቁ 36320 ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አንጻር ለማጣራት ለሰበር

ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ17/12/14ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በ16/3/15ዓ.ም በተጻፈ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ በ4/2/15ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ብይን እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸና እንዲሁም 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው ጭምር ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በ5/4/15ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱተ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ብይን እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 33(2) ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ማናቸውም ሰው ክስ ለማቅረብ አይፈቀድለትም በማለት ደንግጓል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 36320(ቅጽ 9) የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ካርታ በማቅረብ ብቻ የሚረጋገጥ አለመሆኑን የፍ/ብ/ህ/ቁ 1195ን መሰረት በማድረግ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ከላይ ከተጠቀሰው የስነስርአት ህግ ድንጋጌ አንጻር በስር ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ክስ ባቀረበበት ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለው ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ አመልካች ከክሱ ጋር በማያያዝ በሰነድ ማስረጃነት ክስ የቀረበበት ይዞታ በ1963ዓ.ም በግዢ የተገኘ መሆኑን የሚያስረዳ የሽያጭ ውል፤ ስሙ ወደ አመልካች የዞረበትን በ29/10/63ዓ.ም የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ፤ ግብር የተከፈለበት ደረሰኝ፤ ክስ የቀረበበትን ይዞታ በተመለከተ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ 240234 ላይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርቦ በይዞታው ላይ ተከሳሾች እየፈጸሙ ያሉት ተግባር ሁከት ስለሆነ ሊወገድ ይገባል ብሎ ፍ/ቤቱ በ2/10/09ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ እና ሌሎች ማስረጃዎችን ማቅረቡን የስር ክሱ እና ክርክሩ ይዘት የሚያስገነዝብ ነው፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች ደግሞ አመልካች ክስ ባቀረበበት ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑን የሚያስረዱ ሆኖ ሳለ እና ከዚህ አንጻር የስር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የለውም ሲሉ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ወደ ፍሬጉዳዩ በመግባት ክርክሩን መርቶ በአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ላይ የመሰለውን ውሳኔ ሊሰጥ ሲገባው አመልካች የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግስት ንብረት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 47/67 ከወጣ በኋላ ከመንግስት አካል የተሰጠውን የይዞታ ማረጋገጫ አላቀረበም፤ በይዞታው ላይም ግብር እየገበረ የነበረ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም ስለሆነም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 33(2) መሰረት አመልካች መብትና ጥቅም ሳይኖረው የቀረበ ክስ ነው በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ የሰጠው ብይን እንዲሁም ጉዳዩን

በይግባኝ ያየው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤቱን ብይን ከላይ በተገለጸው መልኩ ሊያርም ሲገባው ይግባኙን በመሰረዝ የሰጠውን ትእዛዝ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ለ) እና (ሸ) እንዲሁም አንቀጽ 10(1)(ለ) ድንጋጌዎች መሰረት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበትና ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ 258076 በ24/3/14ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 217574 በ8/10/14ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በተጠሪዎች ላይ በስር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ ባቀረበበት ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም አለው በማለት ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ወስኗል፡፡
3. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የኮ.መ.ቁ 258076 የሆነውን መዝገብ አንቀሳቅሶ ወደፍሬጉዳዩ በመግባት ግራቀኙን በማከራከር እና ተገቢዎቹን ሂደቶች ሁሉ በመከተል ጉዳዩን አጣርቶ እና መርምሮ በአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ላይ የመሰለውን ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡
4. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
6. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ